የወንድም ዱዓ ዋጋ

ሰሻል ሚዳያው የብዙ ነገሮች መተንፈሻ ከሆነ ቆይቷል። አንዳንዱ እሱ ብቻ በሚያወቀው ጉዳይ ብድግ ብሎ ሒንና ሊልላህ ወኢንና ኢለይሂ ራጂዑንኒ ይላል። ከዚያ አንባቢ ምን ሆነ? ምን ተከሠተ ብሎ በጥያቄ ይረባረባል። ለላው በግል ጉዳይ የገጠመውን ሥም ሳይጠቅስ በነገር ሽንቁጣ ይፖስታል። ጠያቂው ማንን ነው ብሎ ይመጣባል። ከሰልከ በኋል፣ ካለመግባባት በኋላ፣ ከወገዘግብ በኋላ ሰውን አለያም በድንን አሰመልከተው ሚለጠፉ ብዙ ነገሮች አሉ። ከሲድብ እስከ አሸመር፣ ከዱዓ እስከ እርግማን፣ ከነቆራ እስከ ዘለፋ... የፌስቡክ ግድግዳ ይሆን ሁሉ ይችላል። ጉደኛ መሬት ሆኗል።

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ሐዘናቸውንና ብሥታቸውን ሰው ሁሉ ሊያያቸው በሚችል ሁኔታ በዚሁ ግድግዳ ላይ መጥተው ይተነፍሳሉ። ሲተነፍሱም አይፈሩም፣ አያፍሩም። ሲፈልጉ ደስታቸውን በምስጋና ይገልፃሉ። ሲሻቸው ይራገማሉ። ያ ረብ! እያሉ ዱዓ የሚያደርጉም አሉ። የፈለጉትን ነገር በነፃነት ይለምናሉ። አንዳንዴ የነዚህን ሰዎች ትንፋሽ የማይወዱ አሊያም የማይመቻቸው ሰዎች እንዳሉ አስተውላለሁ። በሁኔታቸው እነርሱ የተለመኑ ይመስላሉ። እንደ ለማኝ አድርገው በቁጣና በማሸማቀቅ ለማባረር የሚሞክሩም አሉ "ሂዱና ወደ አላህ ተንፍሱ እዚህ መጥታችሁ ብሥታችሁን አታራግፉብን" በማለት የሚተፉትን አያለሁ።...

"እንዲህ ሆነን፣ እንዲያ ደረሰብን..." ብለው አለቃቅሰው የሚጽፉትንም "እኛ ምን እናድርግ ታዲያ?" ብለው የሚጠይቁም አሉ። ከመጠየቅም አልፈው የሚበሳጩም ይኖራሉ።

ግና ሃሳቤ ከዚህ የተለየ ሆነብኝ። በበኩሌ ፌስቡክም ሆነ ሌላ ነገር ላይ የሆነ ነገር ጽፌ ወይም አድርጌ በምላሹ ዱዓ ከተደረገልኝ በአስተያየት መስጫ ቦታው ላይ ባላሰፍርም ከልቤ በውስጤ "አሚን" ሳልል ያለፍኩበት ጊዜ የለም። የጨነቀው ሰው "ዱዓ አድርጉልኝ" ብሎ ሲለጥፍም በሃሳብ መስጫው ላይ መልዕክቴን ባላሰፍርም ከልቤ ዱዓ ያላደረግኩለት የለም። አንድ ሙስሊም ለወንድም አህቱ በአደራ መልክ ከሚለምናቸው ነገሮች መካከል "ዱዓ አድርጉልኝ" ነው። ስለዚህ "በዱዓ አስቡን" ያሉትን ሁሉ በቅንነት ልናገለግላቸው ይገባል። አላህ የማስታወስ ልቦናውን በስጠን ጊዜ "አቦ አምላካችን አላህ ሃሳቡን ያንሳለት፣ ምኞቱን ያሳካለት፣ ከጭንቀቱም ይፈርጀው፣ ይፈርጃት..." ማለት ይኖርብናል። እንዲህ በማለታችን ዋንኞቹ ተጠቃሚዎች እኛው ነን። ለሰዎች ዱዓ ስናደርግ አጠገባችን ዱዓ ተቀባይ መላኢካ መኖሩን እንዴት እንዘነጋለን!። ስለዚህ ለሌላ ዱዓ የሚያደርግ ሰው በተዘዋዋሪ ለራሱ ዱዓ እያደረገ ነው ማለት ነው። ይህንን በሚገባ ማስተዋል ያስፈልጋል።

የኔ ቢጤዎች በመንገድ ላይ ሲለምኑን አንዳንድ ጊዜ ሳንቲም ሳንሰጣቸው እናልፋለን። ምክንያታችን ደግሞ አቅም ማጣት አሊያም ንፉግነት ሊሆን ይችላል። ከሩቅ ሆነው ሳያውቁንና ሳናውቃቸው ዱዓእ አድርጉልኝ፣ ጉዳዬን ለፈጣሪዬ ንገሩልኝ፣ ለኔ ስትሉ እጃችሁን ዘርጉልኝ፣ ምላሳችሁን አንቀሳቅሱልኝ፣ በልባችሁ አስቡኝ... ብለው በፊሴቡክ አደባባይ በግልጽ የወጡትን ግን በምን አንጀታችን እናልፋቸዋለን!። እሩቅ ያለ የወንድም/እህት ዱዓእ ምላሽ እንደማይነፈገው ስናስታውስ ደግሞ ተስፋችንን ከፍ እናደርጋለን። ዱዓ ለማድረግም እንነሳሳለን። በኛ ዱዓ የሚያተርፍ አንዳለ ካወቅን ይህንኑ አስበን እጃችንን ለአገሌ/አገሊት ስንል መዘርጋት ይኖርብናል።

ዛሬ ላይ ዱንያ ያላደከመችው ሰው ማን አለ ወዳጆቼ!... አንዳንዱ ሥጋው ታሟል፤ ሌላው መንፈሱ ታሟል። ትዳሩ የታመመ፣ ቤተሰቡ የታመመ፣ ኑሮው የታመመ፣ ሥራው የታመመ፣ አዕምሮው የታመመ... ብዙ አለ። ዱንያ ህመሟ ብዙ ነው። እህ.. ብለን ብናዳምጠው ያልጠበቅነውን ጉድ ከወንድም እህት እንሰማለን። ሰዎች ስንባል ሁላችንም የጎደለን፣ ሁላችንም ደካሞች፣ ሁላችንም ፈላዎች፣ ሁላችንም ህመምተኞች ነን። ለነኚህ ሁሉ ህመምተኞችና ለራሳችንም ጭምር ማዘንና እርስ በርስም መተዛዘን አስፈላጊ ነው። በቁሳዊም ይሁን በመንፈሳዊ ጉዳይ ወዶና ፈቅዶ የሰውን እጅ የሚያይ የለም። በዱንያዊ ጉዳይ ሀብታም የሆነው እንዳለው ሁሉ በአላህ ዘንድ ሀብታም የሆነውም እንዲሁ አለ። በአላህ ዘንድ ሀብታም ማለት አላህ ስለትከለኛ ባርነቱ እውቅና የሠጠው ሰው ማለታችን ነው። በዱንያ ጉዳይ ይረዳን ዘንድ ከአላህ በታች የሃብታምን እጅ እንደምናየው ሁሉ፣ በዱዓእ ጉዳይም ወደ አላህ በመድረሱ ሂደት ወንድሞቻችን እንዲያግዙን እንማፀናለን።

አስልምና ትልቅ ፀጋ ነው። ዲናችን ሰፊ ቤት ነው። በዚህ ቤት ውስጥ በአካል ሳናገኛቸው፣ በመልከም ሳናውቃቸው፣ እምነት ያስተዋወቀን፣ የሃሳብ መግባባት ያቀራረበን፣ ዱዓ ብቻ ያስተሳሰረን ብዙ ወዳጆች አለን። ሰው ሆኖ ምን ያደርግልኛል? የት ያውቀኛል? ባውቀው ባላውቀው ምን ይቀርብኛል?... የሚባል ሰው የለም። ሰው ለሰው አጋዥ ነው። በምድር ላይ ድሃ የሚባል ሰው የለም። ገንዘብና ንብረት ባይኖረው በዱዓእ ያግዘናል። ዱዓ ደግሞ ከሁሉም ነገር ይበልጣል። ገንዘብን ጨምሮ ብዙ ነገር ያመጣል። ዱዓ ቀላል ነው እንዴ?!

ከአብራካችሁ እንደወጣ እንደምትሳሱለት ልጅ የዱንያ ሸክም ሁሉ ቅልል ይላችሁ ዘንድ ተመኘሁ። አሚን ካላችሁ ትጠቀማላችሁ።

ለራስ መድረስ

አራት ሰዓት ሆኗል። አራዳ ወረድኩ። ፒያሳ ግንባሯ፤ ቢቢ ሄራ ላይ እንደደረስኩ ፀጉር የራቀው አናቴ እንደ ህፃን ልጅ የራስ ቅል ድከ ድከ ማለት ጀመረ። ነፍሴ በግንባሬ በኩል ልትወጣ ይመስል አጣደፈችኝ። በግራ ጎኔ በኩል መዶሻ የያዘ ወቃሪ አናቴን ሊያፈርሰው ውስጤ የገባ እስኪመስለኝ ድረስ ፋታ ነሳኝ። ድው ድው ድው ...።

እስቤ የወጣሁለት ብዙ ሐጃ አለኝ። መንገድ ላይ አቀር ይኾን ወደ ቤት እመለሰ ይሆን!... እያልኩ አሰላሰልኩ።

ይህን ድንገተኛ ደራሽ አደጋ በምን ልመከተው እያልኩ ሳስብ በግራ በኩል ካለው ቤት የጀበና ቡና ሽታ አወደኝ። እስቲ ልሞክርበት አልኩና ገብቼ ትንሽ ዱካ ሰቤ ተቀመጥኩ። ሰው ሁሉ ጋዜጣና መጽሔት ላይ ተደፍቷል። ያነባል፣ ያነባል፣... ፒያሳ ማለዳ ላይ የንባብ ሰፈር ናት፣ የሸገር ሰውም አንባቢ ነው።

እውጭው ላይ እንደወትሮው ብዙም ግርግር የለም። የከተማዋ ዋና አድማቂዎች በዐረፋ በዓል ምክንያት ወደ አገር ቤት ስለሄዱ ነው መሰለኝ የመርካቶ ጭርታም ለፒያሳ ተርፏል። ቡናዬን ማማሰል እንደጀመርኩ ከጎዳናው "መንግሥተ ሰማያት ደርሷልና ንሰሐ ግቡ!" የሚል ከፍተኛ የአዋጅ ድምፅ ሰማሁ። እነኚህ ሰዎች በዚህ መስመር ለምን እንደማይጠፉ ይገርመኛል። "እኛማ ከገባን ቆየን እኮ" እያልኩ ጎንበስ ብዬ አጉረመርማለሁ። ለቡናው አንዴ ፉት እንዳልኩለት ይሄ አናቴን የያዘው ውቅር በአንድ ስኒ ብቻ የሚፈታ ስላልመሰለኝ "ማኪያቶ ድገሚኝ" አልኳት ለታዛዧ። ስግብግብነት ይሆን! አልኩ በውስጤ።

ቡናውን በአንድ ትንፋሽ እንደጨለጥኩ ማኪያቶው ደረሰልኝ። አከለፍልፌ አወራረድኩት። አሁንም እውጭ ውጭውን እቃኛለሁ። ከመጽሔትና መጽሐፍ አካባቢ የማይጠፋውን ሞለል፣ ደልደል፣ አጠር፣ ከአናቱ ትንሽ ገባ፣ ፊቱ ቀላ ያለ አንድ ወዳጄ ይመጣ ይሆን?... ሱሌ። ትንሽ አየሁት። ዛሬ አልመጣም። ሰሞኑንም ጠፍቷል።

ብዙም አልቆየሁም። አናቴ ሲፈላ ይታወቀኛል። ቅድም በቁሜ ሊደፋኝ የነበረው የራስ ምታት ጥሎኝ የት አባቱ እንደሄደ እንጃለት። ቀለል እያለኝ ተነሳሁ።

ከራሴ ጋር አወራለሁ።

ሕይወት ብርቱ ፈተና ናት። እንዲህ እየታገልክ ችግሯን አንድ በአንድ ካልፈታህ በትንሽ ራስ ምታት ወደኋላ ትመለሳለህ።

ማስታወሻ

ለመልካምነትም ቦታ አለው!

በሆነ ጊዜ የተወሰኑ ሰዎች ለአደን ወጡ አሉ። የሚታደን ጅብ አግኝተው ሲያሳድዱ ሸሽቶ ከአንድ ገበሬ ግቢ ውስጥ ገባ። የገባበትን ያዩ አዳኞች ተከተሉት። ገበሬው ከቤቱ ሲወጣ የሚያለከልክ ጅብ በጓሮው ውስጥ ተመለከተ። እጅግ ሐሩር ነበር። ጅቡ እዚያ ግቢው የተደበቀ መሆኑ ገባው። የመጡ አዳኞች አሳልፎ እንዲሠጣቸው ገበሬውን ጠየቁት። "ከጠላት ሸሽቶ ከሰው ቤት የተጠጋን ጥገኛን አሳልፎ መስጠት ነውር ነው። ኢይ ካላችሁ ደግሞ በቀስቴ ነው የምለቅማችሁ።" አለና በርከከ አለ።

ሰዎቹ ዞረው ሄዱ። ገበሬውም ወደ ጅቡ ተመለሰና አየው። አሳዘነው፣ ጥም የበረታበት ይመስላል፣ ከፉኛ ያለከልካል። ከፍየሉ ወተት አለበና ሠጠው። ጅቡም ጠጣ። ንቃቱም ድካሙም ምልስ አለለት።

ሲመሽ ባላገሩ ሰውዬ በሠራው መልካም ነገር ደስ እያለው ረክቶ ተኛ። ጅቡ ግን አልተኛም። የገበሬውን መተኛት አስተዋለና ጊዜ ሳይወስድ ቶሎ ብሎ ሰፈረበት። ሆዱን ዘረገፈው፤ ደመ·ንፃም መጠጠው።

ጠዋት ላይ የሆነውን ሁሉ የአካባቢው ሰው አወቀ። በገበሬውም ተሳለቀ። የቅበጠቱን ነው ያገኘው አለ። እንዲህም ብሎ ገጠመ።

> ያለቦታው መልካምነት፣ ውለታ ቢስ ያደርጋል
> ለማይገባው ምግብ ማብላት መልሶ ራስን ያስበላል።

ስለ ምርጥ የመጨረሻ ቃል

"ላስት ወርድ" ብዙን ጊዜ ተማሪዎች ከዩኒቨርስቲ ሊመረቁ ሲል የምረቃ መጽሔታቸው ላይ የሚተነፍሷት ቃል ናት። እያንዳንዱ ተማሪ ካለፈው፣ ካለበትና ከወደፊቱ አንፃር ያለበትን ሁኔታ በመገምገም እምቅ እና ጥሩ መልእክት ይኖረዋል ያለው ቃሉን በፎቶው ሥር ያሰፍራል። ያ ተማሪ ከዕለታት አንድ ቀን የሆነ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ የደረሠ እንደሆነ የሱን ሁኔታ ተከታታዮች ያንን ፋይሉን ይፈትሻሉ። "ላስት ወርዱ" ምን ነበር ሊያሉ። "ላስት ወርድህ" በመጠኑም ቢሆን መገለጫህ ነውና።

ማንኛውም ሙስሊም ሁሌም በንግግር ይሁን በተግባር ከመልካም ነገር መራቅ የለበትም። ተሳስቶ እንኳን ሃጢኣት ላይ ቢወድቅ ቶሎ ብሎ ወደ ቀድሞ ቦታው ወደ በጎነቱ ለመመለስ መበርታት ይኖርበታል። ኃጢኣት የጭቃ ውሰጥ እሾህ ነው ሰላም ሊይሰጥም።

ሙእሚን የምድር ላይ ፍፃሜው መቼ እንደሆነ ስለማያውቅ ሁሌም ሁኔታውን ከፈጣሪው ጋር እንዳስተሳሰረ መዘለቅ አለበት ይላሉ ደጋጎቹ። ግዴታ የተደረገበትን ሶላት ይሁን ፆም፣ ዘካ ይሁን ሐጅ አቅሙ እያለው በቸልተኝነት ማዘግየት የለበትም። ዙህር ሳይሰግድ ዐስር ሊደርስበት አይገባም። ዒሻእ ሳይሰግድ እንቅልፍ የሚጥለው መሆን የለበትም። የፆም ቀዷ ያለባት ሴት ቀዷዋን ሳትጨርስ ሌላኛው ረመዷን ዞሮ ሊመጣባት አይገባም። ዝግጁነት ማለት ይሄ ነው፤ ስታንድ ባይ። ሙእሚን ሁሌም ንቁ መሆን ይኖርበታል። ሙእሚን ወደ አኺራው ዓለም ለመጓዝ የሥሙን መጠራት ብቻ የሚጠብቅ፣ ጓዙ ቀለል ያለ ወረፍተኛ ነው። በል ተነስ! ከተባለ ጨርቄን ማቄን ሳይል ያለ ፍራቻ ይነሳል።

በተለይ ድንገተኛ ሞት በበዛበት በዚህ ዘመን ላይ ሰው ከቤት ስለመውጣቱ እንጂ ስለመግባቱ፣ ለጉዞ ስለመሠናበቱ እንጂ መመለሱ ዋስትና የለውም። መተኛቱን እንጂ መነሳቱን እርግጠኛ አይደለም።

ለዚህም ነው ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ለሥራም ሆነ መንገድ ስንወጣ፣ እንዲሁም ስንተኛ የተለያዩ ዚክሮችን ያስተማሩን። ከቤት ስንወጣ በአላህ ተመክተን እንወጣለን። ፈረስ ይሁን መኪና፤ ጢያራ ይሁን መርከብ... ማንኛውም መጓጓዣ ስንሳፈር አላህን እናልቃለን። ስንተኛም "አላህ ሆይ በሥምህ ጎኔን አሳረፍኩ!" ብለን አምላካችንን

ስለ ምርጥ የመጨረሻ ቃል

"ላስት ወርድ" ብዙን ጊዜ ተማሪዎች ከዩኒቨርስቲ ሊመረቁ ሲል የምረቃ መጽሔታቸው ላይ የሚተነፍሷት ቃል ናት። እያንዳንዱ ተማሪ ካለፈው፣ ካለበትና ከወደፊቱ አንፃር ያለበትን ሁኔታ በመገምገም እምቅ እና ጥሩ መልእክት ይኖረዋል ያለው ቃሉን በፎቶው ሥር ያሰፍራል። ያ ተማሪ ከዕለታት አንድ ቀን የሆነ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ የደረሠ እንደሆነ የሱን ሁኔታ ተከታታዮች ያንን ፋይሉን ይፈትሻሉ። "ላስት ወርዱ" ምን ነበር ሊያሉ። "ላስት ወርድህ" በመጠኑም ቢሆን መገለጫህ ነውና።

ማንኛውም ሙስሊም ሁሌም በንግግር ይሁን በተግባር ከመልካም ነገር መራቅ የለበትም። ተሳስቶ እንኳን ሃጢኣት ላይ ቢወድቅ ቶሎ ብሎ ወደ ቀድሞ ቦታው ወደ በጎነቱ ለመመለስ መበርታት ይኖርበታል። ኃጢኣት የጭቃ ውሰጥ እሾህ ነው ሰላም ሊይሰጥም።

ሙእሚን የምድር ላይ ፍፃሜው መቼ እንደሆነ ስለማያውቅ ሁሌም ሁኔታውን ከፈጣሪው ጋር እንዳስተሳሰረ መዝለቅ አለበት ይላሉ ደጋጎቹ። ግዴታ የተደረገበትን ሶላት ይሁን ፆም፣ ዘካ ይሁን ሐጅ አቅሙ እያለው በቸልተኝነት ማዘግየት የለበትም። ዙህር ሳይሰግድ ዐስር ሊደርስበት አይገባም። ዒሻእ ሳይሰግድ እንቅልፍ የሚጥለው መሆን የለበትም። የፆም ቀኗ ያለባት ሴት ቀኗዋን ሳትጨርስ ሌላኛው ረመኗን ዞሮ ሊመጣባት አይገባም። ዝግጁነት ማለት ይሄ ነው፤ ስታንድ ባይ። ሙእሚን ሁሌም ንቁ መሆን ይኖርበታል። ሙእሚን ወደ አኺራው ዓለም ለመጓዝ የሥሙን መጠራት ብቻ የሚጠብቅ፣ ጓዙ ቀለል ያለ ወረፍተኛ ነው። በል ተነስ! ከተባለ ጨርቄን ማቄን ሳይል ያለ ፍራቻ ይነሳል።

በተለይ ድንገተኛ ሞት በበዛበት በዚህ ዘመን ላይ ሰው ከቤት ስለመውጣቱ እንጂ ስለመግባቱ፣ ለጉዞ ስለመሠናበቱ እንጂ መመለሱ ዋስትና የለውም። መተኛቱን እንጂ መነሳቱን እርግጠኛ አይደለም።

ለዚህም ነው ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ለሥራም ሆነ መንገድ ስንወጣ፣ እንዲሁም ስንተኛ የተለያዩ ዚክሮችን ያስተማሩን። ከቤት ስንወጣ በአላህ ተመክተን እንወጣለን። ፈረስ ይሁን መኪና፤ ጢያራ ይሁን መርከብ... ማንኛውም መጓጓዣ ስንሳፈር አላህን እናልቃለን። ስንተኛም "አላህ ሆይ በሥምህ ጎኔን አሳረፍኩ!" ብለን እምላካችንን

እናወሳለን። ሁሌም ከአላህ ጋር መሆን ፍፃሜን ያሳምራል። ለጀነትም ያበቃል። ማስረጃውም የሚከተለው ሐዲሥ ነው-

ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) "የመጨረሻ ንግግሩ 'ላ ኢላህ ኢልለላህ' የሆነ ሰው ጀነት ገባ።" ብለዋል። That must your last word forever!!

እዎ ለታላቅ ስኬት እንበቃ ዘንድ ይህች ቃል ምድር ላይ የመጨረሻ ቃላችን ልትሆን ይገባል። ቃሏ ግን እንዲሁ በዘፈቀደ ማንም የሚያሳካት አይደለችም። ዐረብኛ የቻለ ሰው ሁሉ የሚናገራት ቃል አይደለችም። ይህቺን ቃል ከምድር ሊሰናበቱ ቋፍ ላይ እያሉ ለመናገር ከሏ ጋር መኖር ግድ ይላል። በምላስ ላይ እንዳኖሯት መዋል ማደርን ይጠይቃል። ከሏ ጋር ለረጅም ዘመናት በንግግርም በተግባርም መኖር ያስፈልጋል። ቃሏን ለማለት የሚታደሉት ከአላህ ጋር በትክክል የኖሩ እውነተኛ የአላህ ሰዎች ብቻ ናቸው።

አላህ ይወፍቀን።

ማስታወሻ

'ረጅም ጉዞ አለብኝ' ብለህ ትልቅ ዓላማ ይዘህ የምትንቀሳቀስ ዓይነት ሰው ከሆንክ፣ በጉዞህ ላይ ሊያሰናክሉህ የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ ጥለህ ተንቀሳቀስ። ብቻየን እፈራለሁ ብለህ ከመንቀሳቀስ ወደኋላ አትበል። ብቻህንም ቢሆን ተንቀሳቀስ። አንዳንድ ጊዜ ሰው ማብዛት ለመቅረት ምክንያት ማብዛት የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። ብርቱዎችን ካገኘህ አንድ ሁለት ሰው በቂ ነው። ካልሆነ ሌሎችን አትስማ። የሚጎትቱ ሰዎችን፣ የሚያሰንፉ ሰዎችን፣ ጥሩ ጥሩ የማያስቡ ሰዎችን፣ ተስፋ የሌላቸው ሰዎችን፣ ጥሩ ነገር የማይታያቸው ሰዎችን፣ ተጠራጣሪ ሰዎችን፣ ወሬያቸው ስለ ሰው ብቻ የሆነ ሰዎችን፣ ፈሪ ሰዎችን፣ ላለመሥራት ምክንያት የሚያበዙ ሰዎችን፣ ለዚህም ለዚያም እንከን የሚፈልጉ ሰዎችን፣ ይህንንም ያንንም የሚያነውሩትን፣... አራግፈህ ተንቀሳቀስ። እዚያው ባሉበት አቧራ ይሸፍናቸው ተዋቸው። ቀንና ጨለማ ምንም ሳይሠሩ ዞሮ ይመለስባቸው። ዓላማህ ከፍ ብለህ መብረር ከሆነ ወደነርሱ አትመልከት። ለመንቀሳቀስ አታመንታ። ዋጋ የላቸውምና እነርሱን ስትጠብቅ አታርፍድ። እነርሱ ከፍ ለማለት በተንደረደርክ ቁጥር ወደታች የሚጎትቱ ከባባድ "ድንጋዮች" ናቸውና ከመብረርህ በፊት አራግፋቸው። ድንጋይ ምን አሸከመህ ወዳጄ። ቀለል ብሎህ አየሩን የምትቀዝፈው፣ ክብደትህ ሲቀንስ ነው ወዳጄ። ምድር ላይ መስሚያህ ጥጥ የሆነ ጆግና ካልሆንክ፣ ጠልፎ ጣዩና ህልም ሰራቂው ብዙ ነው ወዳጄ!!